የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፳፬
አዲስ አበባ-መጋቢት ፩ ቀን ፲፱፻፺፰

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

12th Year No. 24
ADDIS ABABA – March 10th 2006

## ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፳፬/፲፱፻፺፰
የማዕድን ሥራዎች ደንብን ለማሻሻል የወጣ
የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ .................ገጽ ፫ሺ፬፻፯

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፳፬/፲፱፻፺፰ የማዕድን ሥራዎች ደንብን ለማሻሻል የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፩/፲፱፻፺፰ አንቀጽ ፭ እና በማዕድን አዋጅ ቁጥር ፶፪/፲፱፻፹፭ አንቀጽ ፶፮ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ «የማዕድን ሥራዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት (ማሻሻያ) ደንብ ቁጥር ፩፻፳፬/፲፱፻፺፰» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. ማሻሻያ

የማዕድን ሥራዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፹፪/፲፱፻፹፮ እንደተሻሻለ እንደገና እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

፩/ በደንቡ አንቀጽ ፪ ሥር የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፭) እና (፮)ተጨምረዋል።

"፭/ 'የኢንዱስትሪ ማዕድናት' ማለት በፋብሪካ ሥራ ሂደት አልፈው ጠርሙስ፣ ወረቀት፣ ሲሚንቶ፣ ማዳበሪያና ለምግብነት ወይም ለሌላ ዓላማ የሚውል ጨው የመሳሰሉ የፍጆታ ዕቃዎችን ለመፈብረክ በጥሬ ግብዓትነት ጥቅም ላይ የሚውሉና ለኃይል ማመንጫነት የሚያገለግሉ በተፈጥሮ የሚገኙ ጠጣር ማዕድናትን ሁሉ ያጠቃልላል፤

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

## CONTENTS

Council of Ministers Regulation No. 124/2006
Mining Operations Council of Ministers /Amendment/ Regulation ........................................ Page 3407

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION NO. 124/2006 COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS TO AMEND THE MINING OPERATIONS REGULATIONS

These Regulations are issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 471/2005 and Article 56 of the Mining Proclamation No. 52/1993.

1. *Short Title*

These Regulations may be cited as the " Mining Operations Council of Ministers (amendment) Regulations No. 124/2006".

2. *Amendment*

The Mining Operations Council of Ministers Regulations No. 182/1994 as amended is hereby further amended as follows:

1/ The following new Sub- Article (5) and (6) are added under Article 2 of the Regulations:

"5/ 'industrial minerals' means all naturally existing solid minerals eventually used as raw materials for industrial process to manufacture goods such as glass, paper, cement, fertilizer and edible or other salt and for power generation;

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80001

፮/ ' በከፊል የከበሩ ማዕድናት' ማለት በአዋጁ አንቀጽ ፪(፲፰) የተመለከቱትን ሳይጨምር ሌሎች ማናቸውም በተፈጥሮአዊ ግኝታቸው ለማስዋቢያነት የሚውሉ ወጥ ወይም በተፈጥሮአዊ አንድነት የተጣመሩ እንደ ኦፓል፣ ሮዶላይት፣ ጋርኔትና ኦሊቪን የመሳሰሉ እንዲሁም ሚኒስቴሩ በመመሪያ በከፊል የከበሩ ማዕድናት ብሎ የሚሰይማቸው ሌሎች ተመሳሳይ ማዕድናት ናቸው::»

፪/ የደንቡ አንቀጽ ፮ ንዑስ አንቀጽ (፪)፣ (፫) እና (፬)፣ ተሰርዘው በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) ተተክተዋል፤

"፪/ ፈቃድ ሰጭው ባለስልጣን ፈቃድ ለማግኘት የቀረበውን ማመልከቻ ከመዘገበ በኋላ ወዲያውኑ በአመልካቹ የቀረቡትን መረጃዎች በሙሉ አጣርቶ ትክክለኛነታቸውን ያረጋግጣል::

፫/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የፈቃድ ማመልከቻዎችንና የተሰጡ ፈቃዶችን የሚያሳይ መዝገብ አዘጋጅቶ ለሕዝብ ክፍት ያደርጋል::"

፫/ የአንቀጽ ፯ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ተሰርዘው በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ተተክተዋል፤

"፩/ ማናቸውም ሰው የተጠየቀው ፈቃድ እንዳ ይሰጥ ወይም የተሰጠ ፈቃድ እንዲታገድ ወይም እንዲሰረዝ መቃወሚያውን ከነ ምክንያቶቹ በጽሁፍ ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ሊያቀርብ ይችላል::

፪/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን መቃወሚያው እንደደረሰው ወዲያውኑ መርምሮ ይወስናል::»

፬/ በደንቡ አንቀጽ ፴፫ ንዑስ አንቀጽ (፩) ሥር የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (መ) ተጨምሯል፤
«(መ) በከፊል ለከበሩ ማዕድናት ...........4%»

፭/ የደንቡ አንቀጽ ፴፬ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፴፬ ተተክቷል፤
«፴፬. <u>ሌሎች ክፍያዎች</u>

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፵፱ መሠረት ለምዝገባ ለሚቀርብ ሰነድ ብር ፶ ይከፈላል::

፪/ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት ብር ፳፭ ይከፈላል::

፫/ በአዋጁ አንቀጽ ፶፩ መሠረት ለታዩ ጉዳዮች የውሳኔ ቅጂ ለማግኘት ብር ፳፭ ይከፈላል::

፬/ የፈቃድ ቅጂ ወይም የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ምትክ ለማውጣት ብር ፲፭ ይከፈላል::

6/ 'semi precious minerals' means all minerals or naturally existing mineral aggregate, other than those referred to in Article 2(18) of the Proclamation, that possess intrinsic ornamental value such as Opal , Rhodolite Garnet, Olivine and such other Minerals that the Ministry may, by Directive, so designate."

2/ Sub. Articles (2), (3) and (4) of Article 6 of the Regulations are deleted and replaced by the following new Sub-Articles (2) and (3):

"2/ Immediately following the registration of each application, the Licensing Authority shall verify all information submitted by the applicant.

3/ The licensing Authority shall maintain a register indicating applications and licenses which will be open to the public for inspection.''

3/ Sub-Articles (1) and (2) of Article 7 of the Regulations are deleted and replaced by the following new Sub-Articles (1) and (2):

"1/ Any person may file at the office of the Licensing Authority a written objection to the grant of a license or requesting the suspension or revocation of same.

2/ Upon receipt of an objection, the Licensing Authority shall promptly hear and decide upon the objection."

4/ The following new Sub-Article (d) is added under Sub- Article (1) of Article 33 of the Regulations:
"d) for semi precious minerals .................. 4%"

5/ Article 34 of the Regulations is deleted and replaced by the following new Article 34:
"<u>34. Other Payments</u>

1/ Birr 50 shall be payable for registration of documents in accordance with Article 49 of the Proclamation.

2/ Birr 25 shall be payable for the issuance of a certificate of professional competence.

3/ Birr 25 shall be payable for copies of records of cases heard in accordance with Article 51 of the Proclamation.

4/ Birr 15 shall be payable for a replacement copy of a license or a certificate of professional competence.

፭/ ወደ ውጭ ሀገር የሚላኩ ማዕድናትን ለማስ መርመርና የማረጋገጫ ሠርተፊኬት ለማው ጣት በማዕድናቱ ክብደት መሠረት የሚከ ተለው ክፍያ ይከፈላል፤
ሀ) እስከ ፶ ኪሎ ግራም ................ ብር ፳
ለ) ከ፶ በላይ እስከ ፪፻ ኪሎ ግራም.ብር ፴
ሐ) ከ፪፻ ኪሎ ግራም•በላይ ...... ብር ፵"

፫/ <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሚያዝያ ፳፭ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

5/ The following fees shall be payable for the testing of Minerals and the issuance of verification certificate on the basis of size of shipment of minerals to be exported:
a) up to 50 kg. ............................ Birr 20
b) above 50 up to 200 kg. ........ Birr 30
c) above 200 kg. ...................... Birr 40"

<u>*3. Effective Date*</u>

These Regulations shall enter into force as of the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

*Done at Addis Ababa, this May day of 3, 2006.*

***MELES ZENAWI***
***PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA***

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE